የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
የኢሚግሬሽን ዜግነትና የወሳኝ ኩነት ኤጀንሲ
Immigration, Nationality and Vital Event Agency

ቁጥር Ref. No. ንሠመ/492/2667
ቀን Date 07/9/12

**ለኢንቨስትመንት ኮሚሽን**

**አዲስ አበባ**

**ጉዳዩ፡- ስለውጭ ሃገር ኢንቨስተሮች አስመልክቶ ስለተጻፈው ደብዳቤ መልስ ይመለከታል፡፡**

በዓለማችን ብሎም በሀገራችን በከፍተኛ ሁኔታ እየተዛመተ ባለው (COVID 19) ወረርሺኝ ምክንያት ኤጀንሲያችን ከማርች 24/03/2020 ጀምሮ አስገዳጅ ከሆኑ አገልግሎቶች ውጪ ላልተወሰነ ጊዜ አብዛኛው አገልግሎቶች መቋረጡ ይታወቃል። ይህንንም መሰረት በማድረግ የኢንቨስትመንት ኮሚሽን ለኤጀንሲያችን ሚያዚያ 28/2012 ቀን በተጻፈው ደብዳቤ ኢንቨስተሮች የተለያዩ አገልግሎቶችን ማግኘት እንዳልቻሉ በመግለጽ በኤጀንሲው በኩል መፍትሔ እንዲፈለግ መጠየቃችሁ ይታወሳል። በመሆኑም፤-

- ኤጀንሲው መደበኛ አገልግሎት መስጠት ሲጀምር ከማርች 24/2020 ጀምሮ ጊዚያዊ የመኖሪያ ፈቃድ እና የተለያዩ ቪዛ አገልግሎት እንዲሰጣቸው የሚፈልጉ ባለጉዳዮች ማሟላት የሚገባቸውን ዶክመንት አሟልተው ሲመጡ ከማርች ከ24/2020 ጀምሮ ኤጀንሲው አገልግሎት መስጠት እስከጀመረበት ጊዜ ድረስ ያለውን ቅጣት ሳይከፍሉ የጊዚያዊ መኖሪያ ፈቃድና የቪዛ ክፍያ ብቻ በመክፈል አገልግሎት በማግኘት ላይ ይገኛል።
- የተለያዩ የውጭ ሃገር ዜጎች ከአሁን በፊት የመኖሪያ ፈቃዳቸው የጊዜ ገደቡ ሳይጠናቀቅ ከሀገር የወጡ ባለጉዳዮች ከሀገር ውጭ እያሉ የጊዚያዊ መኖሪያ ፈቃዳቸው እንዲሰረዝ ጥያቄ የሚያቀርቡ ባለጉዳዮች የባለጉዳዮቹን የፓስፖርት ኮፒ፣ የተሰጣቸው ጊዚያዊ መኖሪያ ፈቃድ፣ ፎቶ፤ ከግብር ነፃ መሆናቸውን፤ የበንክ እዳ የሌለባቸው መሆኑን የሚገልጽ ደብዳቤ እና የስም ዝርዝራቸውን የያዘ መረጃ በማቅረብ እንዲሰረዝላቸው

የፈለገው ድርጅት /ተወካይ/ ከኢንቨስትመንት ኮሚሽን ተጨማሪ የድጋፍ ደብዳቤ በማያዝ ***ኤጀንሲው ስራ ሲጀምር*** አገልግሎቱን ማግኘት ይችላሉ።

- በሀገራችን በተፈጠረው በኮረና ቫይረስ (COVID 19) ምክንያት ኤጀንሲያችን የውጭ ዜጎች የጊዚያዊ መኖሪያ ፈቃድ ዕድሳት አገልግሎት እየሰጠ ባለመሆኑ ባለጉዳዮቻችን የባንክ አገልግሎት ለማግኘት ያልቻሉ ኢንቨስተሮች ካለው ወቅታዊ ችግር ***ከኤጀንሲያችን የመኖሪያ ፈቃዳቸው ሳይታደስ የድጋፍ ደብዳቤ ለበንክ በመጻፍ*** ጊዚያዊ አገልግሎቱን ከባንክ እንዲያገኙ ቢደረግ፤
- (COVID 19) ወረርሽኝ በሽታ ምክንያት አዲስ የኢንቨስትመንት ቪዛ አቁመናል ምክንያቱ በውጭ ሀገር የሚገኙ ኤምበባሲዎች ስራ የማይሰሩ በመሆኑ ስለሆነም የE-VISA አገልግሎት ያላቆመ ስለሆነ አዲስ አመልካቾች በ E-VISA አማካኝነት አገልግለት ማግኘት የሚችሉ መሆኑን እየገለጽን ከላይ በተቀመጡት የመፍትሔ አቅጣጫዎች መሰረት **በጊዚያዊነት ተግባራዊ** እንዲሆን እንጠይቃለን።

ከሠላምታ ጋር

IMMIGRATION, NATIONALITY & VITAL EVENT AGENCY

ታምሩ ግንበቶ
ም/ዋና ዳይሬክተር

**ግልባጭ**

- ለዋና ዳይሬክተር
- ለሠነዶች ምዝገባና አሰጣጥ ዳይሬክቶሬት